# የብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

## የባለ አክሲዮኖች አንደኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባ

ታህሳስ 2፣ 2003 ዓ.ም

ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.

BERHAN INTERNATIONAL BANK S

ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

**BERHAN INTERNATIONAL BANK S.C.**

# የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት

## እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 3 ቀን 2009 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2010

ታኅሣሥ 2 ቀን 2003 ዓ.ም.

# የብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት

## 1. አጠቃላይ

የብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የዳይሬክተሮች ቦርድ እ.ኤ.አ. ከጥቅምት 3 ቀን 2009 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2010 ያለውን የባንኩን የዘጠኝ ወራት የሥራ አፈጻጸም ዘገባ የባንኩ ባለቤት ለሆናችሁት ባለአክሲዮኖች በዚህ የመጀመሪያ በሆነው ጉባኤ ሲያቀርብ በታላቅ ደስታ ነው፡፡

ብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ በተፈቀደ 300 ሚሊዮን ብር፣ በተመዘገበ 137 ሚሊዮን ብር እና በተከፈለ 95.7 ሚሊዮን ብር ካፒታል እንዲሁም ከ 6,200 በላይ ባለአክሲዮኖች እ.ኤ.አ ሰኔ 27 ቀን 2009 ሁሉአቀፍ የንግድ ባንክ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን ፈቃድ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመውሰድ መቋቋሙ ይታወሳል ፡፡

ባንኩ በበጀት ዓመቱ ባንኩን በማደራጀትና ሥራ በማስጀመር ለቀጣይ ስኬታማ ጉዞ መሠረት የሚሆኑ በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል ፡፡

ባንኩ ሥራ የጀመረበት ዓመት ዓለም ካጋጠመው የኤኮኖሚ ቀውስ ተጽእኖ የተነሣ በአገሪቱ ኤኮኖሚ ላይ የዋጋ ግሽበትና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ችግሮች የተደቀኑበት ጊዜ እንደነበረ የታወቀ ነው፡፡

የዋጋ ግሽበቱ በራሱ እና ኤኮኖሚውን ለማረጋጋት በመንግሥት የወጡ ገንዘብ ነክ የኤኮኖሚ መመሪያዎች በተለይም የባንኮች የማበደር ጣሪያ መቀመጥ ገና ጀማሪ ለሆነው ባንካችን በአገልግሎት ማስፋፋት እና ትርፋማነት ላይ ቀጥተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳርፏል፡፡

የባንክ ባለሙያዎችን በማፈላለግ እና ባንኩን በሰው ኃይል ማደራጀቱ ፣ ለቅርንጫፍ የሚሆኑ ጽሕፈት ቤቶች በተመረጡ ከተሞችና ቦታዎች በማፈላለግ የመከራየትና አስፈለጊውን የቢሮ መሣሪያዎችን የማዘጋጀት እና ቴክኖሎጂ የማስገባት ሥራዎችን ማከናወን በባንኩ ኢንዱስትሪ እያደገ ከመጣው ውድድር ፣ የቤት ኪራይ ዋጋ መናር፣ የቢሮ ዕቃዎችና መሳሪያዎች እጥረት እንዲሁም የብሮድ ባንድ መስመር በቀላሉ አለመገኘት አንጻር አስቸጋሪና ብዙ ጥረት እና ትጋት የጠየቀ ነበር ፡፡

ሆኖም ግን ባንኩ እነዚህን ፈታኝ የነበሩትን የምስረታ፣ ባንኩን የማደራጀት እና ሥራ የማስጀመር ምዕራፍ አልፎ የተሻለ እና ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ወደ ተዘጋጀበት ቀጣይ ምዕራፍ የተሸጋገረበት ጊዜ ላይ መድረሱን ስገልጽ ደስታ ይሰማኛል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ባንኩ ሙሉ በሙሉ ከኪሣራ ወጥቶ ትርፍ እያስመዘገበ የሚገኝ ሲሆን በቅርቡ ተጨማሪ ቅርንጫፎችን በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች በመክፈት የአገልግሎት አድማሱን ከፍ ያደርጋል፡፡

የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች ከዚህ በመቀጠል በበጀት ፤ዓመቱ ባንኩ ያከናወናቸውን ዋና ዋና ሥራዎች በዝርዝር እንደሚከተለው አቀርባለሁ፤

## 2. የባንኩ ዋና ዋና አገልግሎቶች ክንውን

### 2.1. የተቀማጭ ሂሳብ

ባንኩ እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 ብር 238 ሚሊዮን ጠቅላላ ተቀማጭ ገንዘብ የሰበሰበ ሲሆን፣ ይህም በተቀማጭ ሂሳብ ዓይነት ሲተነተን፤ የተንቀሣቃሽ ሂሳብ ብር 72.8 ሚሊዮን፣ የቁጠባ ሂሳብ ብር 72.9 ሚሊዮን እንዲሁም የጊዜ ገደብ ተቀማጭ ሂሳብ ብር 92.3 ሚሊዮን ነው፡፡

እ.ኤ.አ ሰኔ 30 ቀን 2010 የባንኩ አጠቃላይ የተቀማጭ ሂሣብ ደንበኞች ብዛት 4,516 በላይ ደርሷል ፡፡

### 2.2. ብድር

የባንኩ አጠቀላይ የብድር ክምችት እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2010 ብር 153.2 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ይኸውም ብሔራዊ ባንክ ለባንኩ ያሰቀመጠው የማበደር ጣሪያ ብር 154 ሚሊዮን ሙሉ በሙሉ ተጠቅማል ፡፡